በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስነልሳናዊ ስህተቶች ፍተሻ (በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን የ9ኛና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኪሪነት)

አጠቃሎ

*ይህ ጥናት ያተኮረው በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስነልሳናዊ ስህተቶች ፍተሻ (ኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን የ9ኛና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኪሪነት) በሚል ርእስ በሚሰራው ጥናት ላይ ነው። በዞኑ ውስጥ በአራት ወረዳዎች የሚማሩ በአማርኛ ኢአፍ ፈት የሆኑ ሁልት መቶ ኣርባ (240)ተማሪዎች እና በየትምህርት ቤቱ ኣማርኛን የሚያስተምሩ ስምንት(8) መምህራን እንዲሳተፉ ተደርጓል። **የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ** ባሁኑ ወቅት በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ የአማርኛ ቋንቋን የሚማሩ ተማሪዎች የሚፈፅሙት ከጽኈፈት ጋር የተያያዙ ስህተቶችን ነቅሶ በማውጣት ላይ ያትኮረ ነው። ጥናቱ መጠናዊ እና ኣይነታዊ የኣጠናን ዘዴዎች በመቀየጥ የተጠቀመ ሲሆን የኣጠናን ስልቱም ቅኝታዊ ገለጭ ነው። መረጃዎች የተሰበሰቡት፤ ተጠኚ ተማሪዎችን ኣንቀጽ በማጻፍ ስህተቶችን ነቅሶ በማውጣት፣ የጽሁፍ መጠይቆችን በማስሞላት፣ ተማሪዎችን እና መምህራንን ቃለ መጠይቅ በመጠየቅ እና የቡድን ወይይት በማከናወን ነው። በሁሉም መረጃ መሰብሰቢያዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተጠኚ ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ የጽህፈት ችግር ኣለባቸው። የኣናባቢ እና የተነባቢን ጥምረት በተገቢው መንገድ ኣይጠቀሙም፣ ቃላትን በኣውዳቸው ያለመጠቀም፣ ሰዋስዋዊ ስህተቶች እና በርካታ ተማሪዎች ምንም መጻፍ ኣለመቻል ታይቶባቸዋል። በጽህፈት ወቅት የሚፈጸሙ ስህተቶች ተግባቦት ከማወክም አልፈው ምን ለማለት እንደተፈለገ ፍቺውን መረዳት የሚያዳግቱ ወይም ወዳልተፈለገ ተግባቦት የሚያደርሱ ናቸው። ስለዚህ የአማርኛው ቋንቋ ትምህርት በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት በጥሩ ሁኔታ የሚሰጥበትን በማመቻቸት፤ በቋንቋው የሚማሩ ተማሪዎችም የስነልሳን እና የክሂል ትምህርቶችን በተለየ ሁኔታ በጥልቀት እና በዝርዝር እንዲማሩ ቢደረግ ችግሩ በከፍተኛ መጠን ሊቀንስ ይችላል። በቋንቋውም በተገቢው ሁኔታ ሊገለገሉበት ይችላሉ።*

ቁልፍ ቃላት፣ ኢ-አፍፈት፣ ስነልሳናዊ ስህተቶች፣ የጽህፈት ችግር ፣ተግባቦት ማወክ

An examination of linguistic errors among Amharic Second Language Learners in Amharic Essay Writing; the case of grade 9 and 10 Students of North Shoa Zone, Oromia Region.

Tekalign Lema Getachew Anteneh Befikadu Mebratu

Abstract

This study focused on the study titled "Determining the linguistic errors made by grade 9 and 10 students who are second language learner of Amharic when writing essays. In the study two hundred and forty (240) students and eight (8) teachers who teach Amharic in each school participated from four woredas (Wuchale, Girar jarso, Fiche & Debre Libanos). The study used a combination of quantitative and qualitative research methods (mixed approach) and the research design was descriptive. The data were collected; the students were assessed by writing paragraphs, filling out written questionnaires, interviewing students and teachers, and conducting group discussions. The data collected from all data collection sites indicated that the students had significant writing difficulties. They did not use the correct combination of vowels and Consonant, used words out of context, made grammatical errors, and even many students were unable to write at all. These writing errors not only hinder communication but also make it difficult to understand the meaning of what was meant or lead to unwanted communication. Therefore, by ensuring that Amharic language education is given priority at the primary level and is well-taught; give due emphasis to develop students linguistic and as their writing and speaking skill in depth and in detail, the problem can be greatly reduced. They can used the language appropriately.

Key Words/Phrases: - *Second language learner, Linguistic errors, essay writing problem, mis-communication*

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ የፅሀፈት ክሂል ነው። የመጀመሪያ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመደበኛው ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩታል። በሁለተኛ ቋንቋ ጽህፈትን ተጠቅመው ሀሳብን ለመግለጽ የቋንቋውን ሰዋሰውና ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ያስፈልጋል። ጽህፈት እንደማዳምጥና መናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን አፈፈትም ሆኑ ኢአፈፈት ተናጋሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድና ትምህርት የሚዳብር ነው።

በዚህም የተነሳ የጽህፈት ክሂልን ተማሪዎች በትገቢው ሁኔታ ሊማሩተ። በተጨማሪም አንድ ሰው በጽህፈት አማካይነት ለመግባባት ሲያስብና የሚፈልገውን መልእክት ለተቀባዩ ለማድረስ ሲፈልግ እንደመናገርና ማዳመጥ አጋዥ ስሜታዊና አካላዊ መገለጫዎችን (የፊት ገጽታ፣ ፈገግታ፣ ቁጣ፣ የድምጽ ጫና፣ሀዘን፣ድግግሞሽ ወዘተ -) መጠቀም አይችልም (ደብሬ፥ 1990)።

ከዚህ የተነሳ ፀሐፊው የሚያስተላልፈው መልዕክት ለተቀባዩ ግልጽ እንዲሆንለትና የሚያሻሙ ነገሮችን ለማስቀረት ተማሪዎቹ ጽህፈት ከመጻፋቸው በፊት በጥንቃቄ የተሟላ ዝግጅትና በቂ ልምምድ እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል (Norrish 1992)። ይሁን እንጂ ጽህፈት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢታዩበትም የሰው ልጅ ሃሳቡን ለሌሎች ቀርፆ ለማቆየትና ለማስተላለፍ ይችል ዘንድ የጽህፈት ክሂል ትምህርት እንደሚያስፈልገው ይታመናል። በጽህፈት አማካይነት የሚደረግ የቋንቋ ግንኙነትም በዋነኝነት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ የቃልን፣ የሀረግን፣ የዐረፍተ ነገርን፣ የአንቀጽን እና የድርሰትን አወቃቀር በየደረጃው መማር ክሂሉን ጠንቅቆ ለማዳበር አስፈጊ ነው። የመጻፍ ክሂል የቋንቋ ትምህርቶች አብይ ትኩረት የሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሃሳባቸውን፡ በፅሁፍ አቀናብረው መልዕክት ለማስተላለፍ የተለያዩ ችግሮች ያለባቸው መሆኑ በስፋት ይነገራል።

ይህንኑ የጽህፈት ችግር በማስመልከትም ባዬ (1987) ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረዉን የቋንቋ ትምህርት በሰዋስዉ ላይ ያተኮረ እንደነበረና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በክሂል ዘርፎች ላይ እንዳተኮረ ገልጸዉ ሆኖም ግን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽህፈት በሚታይበት ጊዜ እንኳንስ ትምህርታቸዉን ያልጨረሱት ቀርቶ አስራ ሁለተኛ ክፍልን ያጠናቀቁትም ቢሆኑ ማመልከቻ እና ደብዳቤ መጻፍ የማይችሉበት ደረጃ እንደደረሱና በጥቅሉም ተማሪዎች ከቋንቋዉ ስርዓትም ሆነ ከክሂሉ እንደሌሉበት ገልጸዋል።

ቀድምት ጥናቶች ማለትም Ahansson(1975) እና Norrish(1992) የስህተት ትንተናን አላማ መሰረት ያደረጉ በርካታ ጥናቶች መደረጋቸውን በጥናቶቹ በተደረሰባቸው ውጤቶች በመነሳትም በቋንቋ ትምህርት መስክ አስተዋፆ ያደረጉ አዳዲስ ሃሳቦችን ለመከተል ማስቻሉን ይገልፃሉ። ቀደም ሲል የቀረቡትንና መሰል ጉድፈ ሃሳባዊ መሰረቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደ Corder (1967) ሀሳብ፣ስህተት በሁለተኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች የሚታይ የንግግርም ሆነ የፅሀፈት ችግር እንደሆነ እና ይህ ችግር እንዲከሰት የሚያደርጉ ነገሮች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ በስነ ልሳን መዋቅሮች ላይ የሚታየው ጣልቃ ገብነት ትክክለኛው ቃላት እንዳያፈልቁ ስለሚያደርጋቸው ስህተት ይከሰታል። በቅርቡ አየተደረጉ ያሉ ጥናቶችም ትመሳሳይ ውጤት የሚያሳዩ ናቸው።

የኢቶፒክስ የጽህፈት ስርዓት አናባቢንና ተነባቢን አቅፎ የሚይዝ ስለሆነ የአናባቢዎች በትክክል መገለጽ ሰፊ ድርሻ ሊያበረክት ይችላል:: አናባቢዎች ድምጽ ሰጪ ቅንጣቶች ናቸው:: ምክንያቱም ተነባቢ የሚባሉት ድምጾች በየመፈጠሪያ ቦታቸው ላይ ያለውን የአንደበት አካላት ንክኪ ወይም ጥግግት ወደ ድምጽነት የሚቀየሩት፤ ልቅ የሆኑ አናባቢዎች በሀብለ ድምጾች መርገብገብና በምላስ የተለያየ እንቅስቃሴ በመታገዝ በሚያስገኙት የድምጽ ቅላጼ በመታገዝ ነው:: አለበለዚያ ተነባቢን ለመፍጠር በመፈጠሪያ ቦታቸው ላይ የተነካኩት ወይም የተጠጋጉት የአንደበት አካላት ካለ አናባቢዎች ልቀት በምንም አይነት ሁኔታ ድምጽ ሊያወጡ አይችሉም:: ስለዚህ የቋንቋዎችን አናባቢ ድምጾች በአግባቡ ማጥናት የተነባቢዎችንም ተገቢ የንበት ሁኔታ ይወስነዋል:: በመሆኑም ጥናቱ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅመሟቸውን ዋና ዋና ስነልሳናዊ ስህተቶች ላይ አተኩሯል።

1.2 ሰበበ ጥናት

ኢትዮጵያ ሀገራችን የበርካታ ቋንቋዎችና ባህሎች ባለቤት ከመሆኗም ባሻገር፤ ብቸኛዋ የጽህፈት ቅርጽ ያላት አፍሪካዊት ሀገር በመሆኗ በልዩ ልዩ የቋንቋ ዘርፎችና በጽህፈት ሰርዓቷ ላይ ልዩ ልዩ ጥናቶች ሲደረጉ፤ የስዋስው መጽሀፍትና መዝገበ ቃላት ሲዘጋጁ ቆይተዋል:: ባሁኑ ወቀት በኦሮሚያ ክልል ኣማርኛ አንደ ኣንድ ትምህርት ከኣምስተኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥም፥

ብዙዎቹ ተማሪዎች ሁሉም በሚያስብል ደረጃ ተገቢውን የአናባቢ ንበት አስተካክለው አይጠሩም፤ በአነደበተ ርትዑነት ሀሣባቸውን አይገልጹም፤ ሀሳባቸውን አቀናብረው ለመጻፍ በከፍተኛ ሁኔታ ይቸገራሉ:: ከዚህም ሌላ በአናባቢና በተነባቢ ጥምረት የሚፈጠሩ ቃላትን ፍች ለመረዳት የሚያዳግትበት ሁኔታ እየተከሰተ ነው:: ለዚህ

ጥናት መነሻነት እንዲሆኑ ታስበው ኣጥኚዎች በናሙና ጥናት ወቅት ከ9ኛና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ፅሁፍና ንግግር ከተወሰዱት አብነቶች መካከል የሚከተሉት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው::

(1)የምካራይ ቢት ኣሌ/ይ‰ምክኣርኣይ ብኢት ኣልኤ/

የምሻጢ ባት ኣሌ/ይ‰ምሸኣጥ ብኣት ኣልኤ/

ባዚ ቁጥሪ ዳውሎ/ብኣዝኢ ቅኦጥርኢ ድኣውልኦ/

የሚማሩ /ይ‰ምኢምኣርኡ/~የምመሩ /ይ‰ምም‰ርኡ/ ወዘተ.

እነዚህን መሰል ችግሮት በእለት ተእለት ተግባቦት እና በሚጻፉ ትናንሽ ማስታወቂያዎች በስፋት ይስተዋላሉ። ይህ ችግር ደግሞ ለቋንቋው የተግባቦት እድገት በጣም ፈታኝ ሁኔታ ይፈጥራል:: በቋንቋው የተግባቦት ክፍተት ከመፍጠሩም ባሻገር፤ የቋንቋውንም ገለጻ ሊያዛባው ይችላል በሚል መነሻነት ይህንን ጥናት ለማከናወን ተነስተናል::

1.3 የጥናቱ አላማ

1.3.1 ዐብይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎች በቋንቋ ቋንቋው ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሙት ከስነልሳን እና ከቋንቋ ኣጠቃቀም ጋር የተያያዙ ስህተቶች መተንተን ነው።

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በአማርኛ አፍ ፈት ያልሆኑ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል በቋንቋው የሚማሩ ተማሪዎች ከጽሀፈት አንፃር የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች መለየት።
- በአማርኛ አፍ ፈት ያልሆኑ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል በቋንቋው የሚማሩ ተማሪዎች ከጽሀፈት አንፃር የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምን ያህል እንደሆኑ መመርመር::
- በአማርኛ አፍ ፈት ያለሆኑ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል በቋንቋው የሚማሩ ተማሪዎች የክሂል ትምህርቶችን የሚማሩበት መንገድ (ስነ ዘዴ እና መርጃ መሳሪያዎች) ከጽሀፈት አንፃር የሚረዱ መሆናቸውን መፈተሽ::

2. ክለሳ ድርሳናት

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች

2.1.1. የስህተት ትንተና ምንነት

የስህተት ትንትና የጥናት ዘዴ በቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ የሚከሰተው ስህተት ምንጩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አሉታዊ ሽግግር ብቻ እንደሆነ የሚገልጽ የጥናት መስክ ነበር:: የስህተት ትንትተና ዘዴ በዘመናዊ መልኩ በ1967 ኮርደር በተባለ የተግባራዊ ስነልሳን ምሁር እንደተጀመረ ይታወቃል:: የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበት እና የተተነተኑትም የስህተት ዓይነቶች በተለያዩ ምድብ ዓይነቶች የሚቀመጡበት ዘዴ ነው (Brown፣ 1994:206)::

እንዲሁም የስህተት ትንተና፣ ስህተትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከፋፍሎ ማጥናት፣ የስህተት ምንጮችን ይጠቁማል፤ ስለ ስህተት ያለውን አሉታዊ አመለካከት በማስቀረት ስህተት እንደ አንድ የትምህርት ሂደት ይቆጥራል:: ከዚህም በመነሳት ለስርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን የዕወቅት ደረጃ ለማመልከት ያገለግላል::

እነዚህ ድክመቶች የተነሳበትን ዓላማ በተገቢው መንገድ እንዳያሳካ እና ሊሰጥ የሚችለውን ጠቀሜታ እንዳይሰጥ አግደውታል:: ይሁን እንጂ ድክመቶቹን እና ነቀፌታዎቹን በመቅረፍ፣ ተጓዳኝ የሆኑ ጥናቶችን በማካሄድ ተግባራዊ የስነ-ልሳን ጥናቱ ቀጥሏል፤ ጠቀሜታውም በብዙዎች ዘንድ ተፈላጊ እንደሆነ ተገልጿል::

2.1.2. የስህተት ትንተና አስፈላጊነት

በተማሪዎች ጽሑፍ ላይ የስህተት ትንተና ማካሄድ በርካታ ፋይዳዎች አሉት Duley, et al. (1982፡138-139) የስህተት ትንተና ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ የሚሆንበትን አቅጣጫ ሲጠቁሙ፣ ከስህተት ትንተና ውጤት ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎቹ የቋንቋ መምህራን ናቸው።መምህራን የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት አንዲረዱ ያደርጋል፤ ካገኙትም መረጃ በመነሳት የትኛውን ይዘት በምን አይነት መልክና ለምን ያህል ጊዜ ማስተማር እንዳለባቸው እንዲወስኑ ያግዛል፤ በዚህም የተማሪዎችን ችግር በሚፈታ መልኩ የተደራጀ የማስተማር ሂደት እንዲኖራቸው ያግዛል። የማስተማር ስነ ዘዴውና የማስተማሪያ

መሳሪያዎች ያለባቸውን ችግር እንዲፈትሹ ይረዳቸዋል፤ በሌላ በኩል የቋንቋ ተማሪዎችን ሰዋስው ለማስተማር ስህቶቹን በማደራጀት እንደ መረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

በሁለተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ ተማሪዎች ናቸው። ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ያላቸው እውቀት ምን ያህል እንደሆነ በመጠቆም ጠንክረው ቢሰሩ የትኞቹን ስህተቶች በቀላሉ እንደሚያስወግዱ እና በየትኛው የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ እንደሚገባቸው ያስገነዝባቸዋል። በተጨማሪም ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች መጽሐፍትንና የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ተገልጿል።

2.1.3. የስህተት ምንጮች

ስህተቶች በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጠሩ የየራሳቸውም መከሰቻ እና መንስኤ ያላቸው ክንዋኔዎች ናቸው። ጽሕፈትም ተግባር እንደመሆኑ በዚህ ተግባር ልምምድ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች ይኖሩታል። የጽሕፈት ትምህርት ብዙ ልምምድን ስለ ሚጠይቅ በልምምድ ሒደት ከፊደላት ቅርጽ ጀምሮ እስከ ቃላት አጠቃቀም ድረስ የተለያዩ ስህተቶች ይፈጠራሉ። አንድ ህጻን አፍ መፍቻ ቋንቋውን ሲለምድ ሳይኮላተፍ እንደማይሳካለት ሁሉ ተማሪዎችም የጽሕፈትን ክሂል ለመለማመድ መደናቀፋቸው አይቀርም (LittleWood፣1986፡23) ።

Norrish,(1993፡12-15) ሲገልጹ፣ ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡት ነገሮች ምርጫ፣ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት፣ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡ ምሳሌዎች፣ በምሳሌዎች አማካይነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ወይም ተማሪዎቹ እነዚህን የትምህርት መረጃዎች ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ሊመጡ ይችላሉ።

Dulay,et al.(1982፡96) በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች በጽሕፈት ልምምድ ጊዜ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት ይሆናሉ ብለው ያስቀመጧቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማር ዘዴ ድክመት እና የስነ ልቦና ጉዳዮች ናቸው።

2.1.3.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ

ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖን እንደ አንድ ምክንያት አድርጎ መውሰድን በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል:: ይህንንም ሀሳብ Dulay, et al. (1982:96)፣ Norish, (1983:22) ሲገልጹ፣ ቋንቋን የመማር ሂደት የልምድ ውጤት ስለሆነ፣ በአፍ መፍቻነት የዳበረ የቋንቋ

ልምምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመማር ሂደት ጣልቃ እየገባ በሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ ስህተት ሊፈጸም ይችላል::

እንዲሁም Brown, (1994:263-264) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ መለያ ባህሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ወይም ጣልቃ ገብነት ነው:: የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ለሁሉም ተማሪዎች ዋነኛ የስህተት ምንጭ ነው:: ተማሪዎች ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ከመላመዳቸው በፊት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሰዋስዋዊ ባህሪ በአዕምሯቸው ተቀርጾ ይገኛል:: የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ጽሕፈት ላይ በድምጽ ፣ በቃላት ፣በሀረግ እና በዓረፍተ ነገር አወቃቀር ውስጥ ሊታይ የሚችል ቢሆንም ስህተቱ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው ግን በንበት ላይ ነው::

የአፍ መፍቻ ቋንቋ በታላሚው ቋንቋ ላይ በምን ዓይነት ሁኔታ ተጽኖ እንደሚያስከትል Ngara, (1983:36) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው የታላሚውን ቅርጽ ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ባለው ሁኔታ ይገልጻል:: ይህ ከአፍ መፍቻ ቋንቋው መዋቅር ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ያለው አጠቃቀም፣ ከታላሚው ቋንቋ ትክክለኛ መዋቅር ያፈነገጠ ከሆነ ተማሪውን ለስህተት ይዳርገዋል::ይህንኑ ሃሳብ Jackson,(1987:101) ሲያጠናክሩ፣ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ የተወሰነ ክፍተት ሲያጋጥማቸው ያንን ክፍተት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን መዋቅር ተከትሎ ሊሞሉት ይችላሉ:: ይህ ጣልቃ ገብነት ብዙ ሳይታሰብ የሚከሰት ሲሆን ጎልቶ የሚታየውም ተቀራራቢ ስርዓት ባላቸው ቋንቋዎች መካካል ነው::

2.1.3.2. ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለቋንቋው በተወሰነ ደረጃ ከመጋለጣቸው የተነሳ ያገኟቸውን ጥቂት የቋንቋውን ስርአቶች ይዘው ሃሳባቸውን ለመግለጽ ሲሞክሩ ከታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህሪ ጋር በተያየዘ መልኩ የሚከሰት ስህተት ነው:: ይህም ስህተት ለተማሪዎች ስለ ታላሚው ቋንቋ ህግጋት እና ስርአት በቂ ግንዛቤ ካለማግኘታቸው የተነሳ በተሳሳተ መንገድ በንግግርም ሆነ በጽሑፍ መልዕክት ለማስተላለፍ ሲሞክሩ የሚስተዋል ስህተት ነው:: ይህም ስህተት በውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚመጣ ነው (LittleWood፣ 1986, James፣ 1991, Brown 1994) በማለት ይገልጻሉ::

Dulay, et al. (1982:138-139) እንደገለጹት በውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች የተለያዩ መገለጫዎች እንዳላቸው በመግለጽ እንደሚከተለው ዘርዝረዋቸዋል::

1. ድግግሞሽ:- በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ አንድን የቋንቋ ቅርጽ በሌላ መልኩ መድገሙ የተለያዩ ስህተቶችን ሊያስከትል ይችላል::

2. የተሳሳተ ድምዳሜ:- ተማሪው ለትምህርት የቀረበውን ቋንቋ ህግ ቀደም ሲል በለመደው ህግ አጠቃሎ ለመጠቀም ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት የሚከሰት ስህተት ነው:: በዚህም የተነሣ በታላሚው ቋንቋ ተቀባይነት የሌላቸው ህግጋት ለመጠቀም ሙከራ ሲያደርግ፣ ለተሳሳተ ማጠቃለያ ሊጋለጥ ይችላል::

3. እከላ:- በቦታው አላስፈላጊ የሆነ ድምጽን ወይም ምዕላድን ወይም ደግሞ ቃልን በመጨመር ሊፈጥር የሚችል ስህተት ነው::

4. ግድፈት:- በአንድ አረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ መገኘት የሚገባቸው ተዋቃሪዎች ሳይገኙ በመቅረታቸው ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶች ናቸው::

5. የቅደም ተከተል መፋለስ:- የቋንቋ ስርዓት በሚፈቀደው መልኩ ምዕላዶችን ወይም ቃላት ያለቦታቸው በማስገባት የሚፈጠሩ ስህተቶች ናቸው::

2.1.3.3 የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት

አንድን ቋንቋ ለማስተማር የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ መጽሐፍ፣ መርሃ ትምህርት፣ መርጃ መሳሪያዎች... እና መምህራን የሚከተሏቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ በስህተት ትንተና ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችን በመጠቀስ Norrish, (1992:32) ይገልጻሉ።

የቋንቋ መጽሀፍትን በተገቢው ሁኔታ አለማደራጀት እና ትክክለኛ ይዘቶችን ይዞ አለመገኘት ተማሪዎችን ለስህተት ሊዳርግ ይችላል።ከዚህ አኳያ የማስተማሪያ መጽሀፍት አደረጃጀት እና አወቃቀር እንዲሁም መልመጃዎችን ያቀረቡባቸው ስልቶች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ Richards, (1974:190) ይገልጻሉ። እንዲሁም መምህሩ የሚከተለው የማስተማሪያ ዘዴ እና በክፍል ውስጥ የሚያቀርባቸው መልመጃዎች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ።እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟላ መልኩ ከቀረቡ ተማሪዎችን ወደ ስህተት ሊመሯቸው ይችላሉ። የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪውን ስህተት ሊቀንስ የሚችለው ተማሪዎች የሚጽፉትን እንዲከልሱት በማድረግና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ነው። በመማር ማስተማር ሂደት የጽሑፍ እርማት መስጠት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመቀነስ ያስችላል።እርማት የማይሰጥ

ከሆነ ግን ስህተቱን ከትክክሉ ለይተው ማወቅ ስለማይችሉ ስህተቱን እንደ ትክክል በመያዝ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ይህን አስመልክተው Whitewood,(1980፡106-107) ሲገልጹ፣ ልምድ ብቻውን የቋንቋ ችሎታን አያሳድግም፤ ስህተት እየተበተነ የማይታይ፣ ለስህተቱም እርማት የማይሰጥ ከሆነ የስህተቱ መጠን እየጨመረ ስር እየሰደደ ይመጣል። ስህተት መታረም አለበት ሲባል መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ስህተት ቃል በቃል እየነቀሰ በማውጣት ማረም አለበት ማለት አይደለም። ነገር ግን ተማሪው የራሱን ስህተት በራሱ ማረም የሚችልበትን ዘዴ መፍጠር ነው። ምክንያቱም ተማሪው የራሱን ስህተት በራሱ ነቅሶ ካወጣና ማስተካከያ ከሰጠ፣ ቋንቋውን በተገቢ ሁኔታ ተገንዝቦታል ማለት ይቻላል። ስለዚህ መምህሩ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ተማሪው የሰራውን ስህተት እራሱ እንዲያርመው ቢያደርግ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ያደርገዋል።

Norrish,(1993፡2-16) በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ የመምህሩ የማስተማር ችሎታ ሊለካባቸው ከሚችልባቸው መስፈርቶች መካከል የቋንቋ ትምህርትን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ እና የሚጠቀምባቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማ ማድረግ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው። የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ካልሆነ ተማሪዎች ለስህተት የመጋለጥ እድላቸው የሰፋ እንደሚሆን ያስረዳሉ። እንዲሁም የቋንቋ መርሃ ትምህርት የይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ የቋንቋን ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ማካተት ወይም አለማካተት አንድ ቋንቋ የሚማር ተማሪ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም።

2.1.3.4 ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ተጽዕኖ

ተማሪዎች በጽሑፍ ላይ ስህተት እንዲፈጽሙ ከሚያደርጋቸው ነገር አንዱ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው። በቋንቋ መማር ሂደት ላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለው ጥሩ አመለካከት ትምህርቱን በሚገባ አንዲከታተል የመርዳቱን ያህል፣ በቋንቋውና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ ያለው አመለካከት አሉታዊ መሆን ደግሞ ለመማር ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል። የቋንቋው ኣፍ ፈት ተናጋሪዎች ሌላን ተናጋሪ የሚያስተናግዱበት ሁኔታም የራሱ የሆነ ተጽእኖ ኣለው።ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ሁኔታ ከቤተሰባቸው፣ ከአካባቢያቸው ከጓደኞቻቸውና ከተለያዩ ተላውጦዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ነው። በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ለሚጽፉት ፅሑፍ ያላቸው ትኩረት ይቀንሳል፤ስህተቱም በአንጻሩ ይጨምራል (Norrish 1992:18)።

ስነልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያይዘው ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን፤ ተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ስላለው ሁኔታ በአዕምሯቸው ውስጥ ይዘውት የሚመጡት ነገር በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው Norrish, (1992፡19)። ይህን ሀሳብ Dubin and Olshtain (1986:15) ሲያጠናክሩ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ላይ አሉታዊ አተያይን ከሚፈጥሩ ምክንያቶች አንዱ ከቋንቋው የሚገኘው ጥቅም ነው። በመሆኑም ተማሪው ከቋንቋ ትምህርቱ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ካሰበ ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት በማዳበር ቋንቋውን ለመማር ያለው ፍላጎት ይጨምራል። በዚህም የተነሳ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ይቀንሳሉ። በአንጻሩ ተማሪው ቋንቋውን ከተማረ በኋላ ምንም አይነት ተጨባጭ የሆነ ጥቅም እንደማያገኝ ከተገነዘበ ለቋንቋው ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፤ በጽሑፍ ውስጥ የሚፈጽማቸው ስህተቶችም ሊጨምሩ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ አሉታዊ አተያይ ካለው፣ ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ከሌለው፣ ከቋንቋው ማህበረሰብ ባህል እና ልምድ ጋር የራሱ ባህል እና ልምድ የሚጋጭ ከሆነ፣ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌለው፣ በጽሑፉና በንግግሩ ውስጥ ስህተቶች እየጨመሩ መሄዳቸውን መረዳት ይቻላል። በስህተት ምንጮች ትንተና መላምቶች ውስጥ አራት ዋና ዋና የስህተት ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኦሮምኛ አፈ ፈት ና በአማርኛ ኢ-አፈፈት ተማሪዎች የስህተት ምንጭ ላይ ነው። ብመሆኑም ክአራቱ መላምቶች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት ላይ ትኩረት ያደረጋል።

2.1.8. ስህተትን የመለየት ዘዴ

በስህተት ትንተና ሂደት እስካሁን ድረስ ወጥነት ያለው ስህተትን የመለያ ዘዴ ማግኘት እንዳልቻሉ በትንተናው ዙሪያ በጣም ብዙ የስህተት አይነቶች በመገኘታቸው የተነሳ የስህተቶቹን አይነት መመደቡ አዳጋች እየሆነ እንደመጣ የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ። Dulay,et al.(1982፡246-260) ሲገልጹ በብዙ ባለሙያዎች የሚሰራባቸውንና ለብዙ ጥናቶች የመተንተኛ ዘዴዎች ሆነው ያገለገሉትን አራት የስህተት ትንተና አከፋፈል ዘዴዎች አስፍረዋል።

የመጀመሪያው የስነ ልሳን ክፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ሲሆን ትኩረቱ በስነ-ልሳናዊ የመዋቅር ክፍሎች ላይ ነው። የስህተት ትንተናው በስነ ድምጽ፣ በስነመዋቅር፣ በቃላት አገባብ፣ በስነ-ፍቺና በዲስኩር ጠቋሚዎች ላይ ሊያተኩር ይችላል። በዚህ ዘዴ ስህተቶችን ለመተንተን የሚፈልግ አጥኚ

ስህተትን ከጽሑፍ ውስጥ ከለቀመና ከሰበሰበ በኋለ እንደ የስህተቱ አይነት በተለያየ ስነ-ልሳናዊ ምድብ ውስጥ እያስቀመጠ ይተነትናል። በዚህ ዘዴ አጥኚው አስቀድሞ ለማጥናት ካቀዳቸው የስህተት አይነቶች ውጪ ለሆኑ ስህተቶች ትኩረት አይሰጥም(Dulay, et al.1982፡146-150)።

ሁለተኛው ዘዴ የዓረፍተ ነገር ላዕላይ ቅርጾችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ነው። በዚህ ዘዴ በቋንቋ ለመዳ ሂደት ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የዐረፍተ ነገር አካል የሆነ ቅንጣትን ሊገድፉ ወይም የማያስፈልጉትን ሊጨምሩ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋውን ቅርጽ አላግባብ ሊያሰፍሩ፣ የአንዱን ዓረፍተ ነገር አካል ከሌላው በማስቀደም ቅደም ተከተል ሊያዛቡ፤ ለአንድ አገልግሎት ሁለት ሥርዓተ ነጥቦችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። በመሆኑም ይህ አይነቱ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በዐረፍተ ነገር ውጫዊ መዋቅር ላይ የሚታዩ ስህተቶችን መሰረት ያደርጋል። ይህ ዘዴ ተማሪው ቋንቋ ለመማር በምን አይነት አዕምሯዊ ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍና ቋንቋውን ምን አይነት ዘዴ ተጠቅሞ እየተማረው እንዳለ የሚጠቁም መረጃ ለመስጠት ያገለግላል (Dulay and Burt 1975)። ይህን ዘዴ ከቀደመው ዘዴ የሚለየው አጥኚው ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ከማየቱ በፊት ስህተቶችን ለመመደብ የሚያስችለው የስህተት ምድብ ባለመኖሩ የተነሳ ነው። በመሆኑም በዚህ ስህተት አከፋፈል እና አተናተን ዘዴ አጥኚው ስህተቶቹን የሚመድበው ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መሰረት በማድረግ ነው Dulay, et al.(1982:150-162)።

በሶስተኛነት የሚጠቀሰው ንጽጽራዊ ክፍፍል ሲሆን የስህተት አከፋፈል ዘዴው በታላሚው ቋንቋ አፈ-ፈት እና ኢ-አፈ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳና መማር ሂደት ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በማነጻጸር ነው። ይህንንም Dulay,et al. (1982:153) ሲገልፁ በዚህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በታላሚው ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ከሚፈጽሟቸው ስህተቶች ጋር በምን እንደሚመሳሰሉና በምን እንደሚለያዩ ጥናት ያደርጋል ።

የመጨረሻው የስህተት መለያ ዘዴ ተግባቦታዊ ተጽዕኖን መሰረት ያደረገ የስህተት ክፍፍል ነው። በዚህ ዘዴ ስህተቶች የሚከፋፈሉት ተግባቦትን ከማወካቸው አንጻር ነው። ይኸውም ተማሪው የሚጽፋቸውን ሃሳቦች አንባቢ የማይረዳቸው ከሆነና ግልጽነት ከጎደላቸው የተግባቦቱ ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል። በመሆኑም ይህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የሚያተኩረው ተግባቦትን የሚያደናቅፉትንና የማያደናቅፉትን ስህተቶች ለይቶ መተንተን ላይ ነው። በዚህ የስህተት አከፋፈል ዘዴ የትኞቹ ስህተቶች ናቸው አንባቢው መልዕክቱን እንዳይረዳ እንቅፋት የሚሆኑት የሚለው ጥያቄ በግልጽ ተብራርቶ የተቀመጠ አይደለም (Dulay,et al. 1982 ፡189-90)።

በሌላ መልኩ ከላይ Dulay,et al.(1982፡ ያቀረቡትን አራቱን የስህተት አከፋፈል ዘዴዎች በውስጡ ባካተተ መልኩ Norrish,(1983፡81-92) ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ እና የተፈጸሙ ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ በማለት በሁለት አበይት ምድቦች አስቀምጠውታል።

ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ተማሪው በአብዛኛው ሊፈጽማቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡት ስህተቶች ላይ በመመስረት የስህተት ምደባው እና ትንተናው የሚካሄድበት ስልት ነው። በዚህ ዘዴ የስህተቶቹ አይነት አስቀድሞ የተወሰነ በመሆኑ በተማሪው ድርሰት ውስጥ የታዩት ስህተቶች በተወሰነላቸው ምድብ ውስጥ ይካተታሉ። ይህ ዘዴ ቀላል ና ጊዜ ቆጣቢ በመሆኑ በብዙ አጥኚዎች ተመራጭ ሆኗል።

ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ ስህተቶች ራሳቸው የስህተት ምድባቸውን አንዲወስኑ የሚያደርግ ነው፤ መሰረት የሚያደርገውም በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚገኙትን ስህተቶች ነው። በመጀመሪያ እያንዳንዱ ስህተት በካርድ ላይ ይመዘገባል። ቀጥሎ ካርዶቹ እንደያዙት የስህተት አይነት በየክፍሎቻቸው ይመደባሉ።ክፍሎቹ ባላቸው ተመሳሳይነት አንዱ በሌላው ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል። በዚህ መልኩ በተቻለ መጠን ስህተቶቹን በአነስተኛ ምድብ ውስጥ ለማጠቃለል ይሞከራል። ከዚያም እንደሚያሳዩት ባህሪ ትንታኔው ይካሄዳል።

3. የጥናቱ ዘዴ እና ንድፍ

ይህ ጥናት ገላጭ ስነልሳናዊ ጥናት ሲሆን የአይነታዊ እና መጠናዊ ዘዴን በማጣመር (ቅይጥ) ዘዴን ተከትሏል:: አይነታዊው ዘዴ በአማርኛ የሚማሩ በቋንቋው ኣፍፈት ያልሆኑ የዘጠነኛ እና የኣስረኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰሯቸውን ከጽሀፈት ጋር የተገናኙ ስህተቶችን ፈትሿል፤ ገለጻም ተሰጥቷል። በሌላኛው የሰነድ ፍተሻ እና የመጠናዊ ዘዴ በመጠቀም ኢ-አፈፈት ተማሪዎች ከድርሰት ፅሁፍ አንፃር በቋንቋው ክሂሎች ትግበራ ላይ የሚታይባቸው ተግዳሮት ቋንቋን ከመማር እና ማስተማር ቃለነቢቦች አንፃር መርምሯል:: በመጠናዊው ዘዴ የተጠኚ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሁኔታ፣ በትምህርቱ ክጽህፈት ጋር ያለው ግንኙነት፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተፅዕኖ የመሳሰሉት ሁኔታዎች ተጠንተው እና ተለይተው ወጥተዋል::

3.1. የጥናቱ አካባቢና ተጠኚዎች ንሞና

3.1.1. የጥናቱ ኣካባቢ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት በአማርኛ አፍ-ፈት ያልሆኑና በኦሮምያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ የሚገኙ በ2015 ዓም 9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሆኑ ተማሪዎች ናቸው:: በእነዚህ ተማሪዎች ላይ ትኩረት የተደረገበት ምክንያት ቋንቋውን ከ5ተኛ ክፍል ጀምረው ሲማሩት በመቆየታቸው በዚህ ደረጃ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ሀሳበቸውን መግለጽ ይችላሉ ተብሎ ስለሚገመት ነው:: በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት የቋንቋ ክሂል እና የስነልሳን ትምህርት ዘርፎችን በመማር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመጨረስ የተቃረቡ ተማሪዎች መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ነው::

3.1.2. የተጠኚዎች እና የትምህርት ቤቶች ንሞና

በዞኑ ከሚገኙ 16 ወረዳዎች መካከል ጅዳ፣ ውጫሌ፣ ግራር ጃርሶ እና ደብረሊባኖስ ወረዳዎች እንዲሁም የፍቼ ከተማ ኣስተዳደር ባመቺነት የንሞና ስልት ተመርጠዋል:: ከእያንዳንዱ ወረዳ ኣንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በእጣ ተመርጧል (ብዙዎቹ ከኣንድ በላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኣላቸው ፍቼ ከተማ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስላሉት ሁለቱ ተመርጠዋል):: ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ማሳተፍ ኣስቸጋሪ ስለሚሆን በየወረዳው ከተመረጠው ትምህርት ቤት ከየክፍል ደረጃው አስር ወንድ እና አስር ሴት በድምሩ ሁለት መቶ አርባ ተማሪዎች በእጣ ተመርጠው ለድርስት መጻፍ ፈተና እና ለጽሁፍ መጠይቅ እንዲሳተፉ ተደርጓል:: ከተመረጡት ተማሪዎች መካከል ሁለት መቶ አርባ የሚሆኑት የፅሁፍ መጠይቁን ሞልተው ሲመልሱ ሁለት መቶ ሃያ ስድስቱ ተማሪዎች ድርሰት ፅፈዋል። መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል ለትንተና ብቁ ሆኖ የተገኙት ሁለት መቶ ስላሳዎቹ ብቻ ናቸው። እንዲሁም ከየክፍሉ የሁለት ወንድ እና ሴት ተማሪዎች ደብተር በብድግ ብድግ ተወስዶ በደብተራቸው ውስጥ የሚገኘው ስህተትም ተፈትሿል::

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት ተገቢውን ግብኣት የሆኑ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት፣ በፈተና፣ ተሰብስበዋል:: በእያንዳንዱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኘው መረጃ ከጥናቱ አላማ አንፃር በመልክ በመልኩ ተደራጅቶ በመዛመድ በቀጣይ ምዕራፍ ተተንትኗል::

1.2.1 የፅሑፍ መጠይቅ

በተለያዩ ሙሀራን ማለትም፡ Corder 1974፣Richards & Simpson 1974፣ Jackson 1981፣ Richards፣ 1971) ቅቡልነት ያገኙ የስህተት ምንጮች መተንተኛ መስፈርቶች በመጠቀም በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች ስለድርሰት ፅህፍት መሰረታዊ ግንዛቤያቸውን የሚለኩ፥ ለቋንቋው ያላቸውን አመለካከት፥ ስለማስተማሪያ ዘዴውና የክፍል ውስጥ አተገባበሩ፥ የማስተማሪያ መፃህፍቱ የድርሰት ክሂላቸውን ለማሳደግ ወይም ለመቀነስ ያለውን አስተዋፅኦ በተመለከተ ሁለት መቶ አርባ ተማሪዎች ላስራ ላራት (14) ጥያቄዎች ያለው የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። ሆኖም ግን ለትንተና ብቁ ሆነው የተገኙት ሁለት መቶ ሰላሳዎቹ ብቻ ናቸው።

3.2.2 ድርሰት ማጻፍ

ለጥናቱ ከትምህርት ቤቱ የተመረጡት ተማሪዎች ያለባቸውን ከአማርኛ ድርሰት እና አናባቢዎች ጋር የተገናኘ ስህተት ለመፈተሽ ከተጠኚ ተማሪዎች ውስጥ በዕጣ ንሞና የተመረጡ ተማሪዎች በቃል እንዲፅፉ በማድረግ ማስታወሻዎችን ሰብስቦ የፅሁፋቸውን ደረጃ/ሁኔታ ተፈትሸዋል: በመሆኑም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሁለት መቶ አርባ ተማሪዎች ለምርጫ ከቀረቡላቸው አምስት የድርሰት መፃፊያ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል በመምረጥ በአንዱ ላይ እንዲፅፉ ተደርጓል፤ ሆኖም ግን ድርሰቱን መፃፍ የቻሉት ሁለት መቶ ሃያ ስድስቱ ብቻ ናቸው።

3.2.3. ቃለ መጠይቅ

የጽህፈት ማስተማሪያን አና የስህተትን መፈጠር ሁኔታ ቃለነቢቦች ምሰረት ያደረጉ ስምንት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በትምህርቱ ወቅት የነበረውን የችግር ስፋት ለመረዳት ከስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተመረጡ ቁልፍ መረጃ አቀባይ (ኣንድ ወንድ እና ኣንድ ሴት) መምህርት በጥቅሉ አስራ ሁለት መምህራን ቃለ መጠየቅ ተደርጎላቸው መረጃ ተወስዷል። ከየከፍሉ ለተመረጡ ሁለት ሁለት ተማሪዎችም ኣምስት ጥያቄዎች ለቃለ መጠይቅ ቀርበው መረጃ ተሰብስቧል። የመጠይቆች መሰረታዊ ዓላማም ተማሪዎች ድርሰት በሚፅፉበት ወቅት የሚፈፅማቸውን ስህተቶች፥ የስህተቶችን ምንጭና የመፍትሄ እርምጃዎችን በተመለከተ ትኩርት የሚያደርጉ ናቸው።

3.2.4. የተተኪሪ ቡድን ውይይት

እያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ አንድ የተተኪሪ ቡድን ውይይት በጠቅላላው ከስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስድስት የተተኪሪ ቡድን ውይይት ተደርጓል:: የቡድን ውይይቱ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ ከሚገኘው ሀሳብ እና ከድርሰቶቹ በገሀድ ከሚገኘው ውጤት ጋር ለማነጻጸር ይረዳል:: ዉጤቱም ለጥናቱ አስፈላጊ በሆነ መልኩ/መጠን እየታየ በዚህ ወቅትጠቃሚውን በመውሰድ በስርዓቱ ተገልጸዋል:: በሌሎች መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ከተገኙ ዉጤቶች ጋር ተሰናስሎ እንደአስፈላጊነቱ ለጥናቱ በሚያግዝ መልኩ ከቡድን ውይይቱ የተገኘው መረጃ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል::

3.3. የመረጃ ትንተና

ይህ ለዚህ ጥናት ሲባል የተሰበሰቡ የተለያዩ መረጃዎች በፈርጅ በፈርጅ ተለይተው የተተነተኑበት ክፍል ነው:: በዚህ ውስጥም በመረጃ ሰጭነት የተሳተፉ አካላት ስብጥር፣ በጽሁፍ መጠይቅ መሳሪያነት፣ በቃለመጠይቅና በተተኪሪ ቡድን ወይይት የተገኙ መረጃዎች፣ እንዲሁም ተጠኚዎች ለሙከራ እንዲጽፉ ከተደረጉት ጽሁፎች ላይ የተገኙ ሀጸጾች በመልክ በመልካቸው እንዲተነተኑ ተደርጓል::

በቃለ መጠይቅ እና የተተኪሪ ቡድን ውይይት በማድረግ የተገኙ አይነታዊ መረጃዎች ለጥናቱ ባላቸው ተገቢነት መሰረት በአይነት በአይነታቸው ተደርጀተው ተተንትነዋል: በፅሁፍ መጠይቅ የሚሰበሰቡት መረጃዎቹ፣ በማህበራዊ ሳይንስ ስታስቲካዊ ማእቀፍ (የቀመራዊ ማደራጃ ጥምረት) በ23ኛው ተርታ (SPSS Version 23) ተመዝግበው በመጠናዊው ቀመር ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል:: በዕጣ ንሞና በእያንዳንዱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኘው መረጃ ለጥናቱ በሚጠቅመው መጠን እየታየ ተደራጅቷል:: አንደኛው መረጃ ከሌሎች ውጤቶች ጋር ባለው ተመሳስሎ እና ተቀራራቢነት መሰረት በሶስትዮሽ እየተዛመደ በማነፃፀር ተተንትኗል::

4 ፡- የመረጃ ትንተና

ይህ ክፍል የጥናቱ ተተኪሪ ከሆኑ ከስድስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡ ተጠኚዎች ስብጥር፣ በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃለመጠይቅና በተተኪሪ ቡድን ወይይት የተገኙ መረጃዎች፣ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንዲሁም ተጠኚዎች ለሙከራ እንዲጽፉ ከተደረጉት ጽሁፎች ላይ የተገኙ ሀጸጾች በፈርጅ በፈርጅ ተለይተው የተተነተኑበት ክፍል ነው።

4.1 የዓይነታዊ መረጃዎች ትንተና

4.1.1. ከቃለ መጠይቅ እና ከተተኪሪ ቡድን ውይይቶች የተገኙ የተጠቃለሉ ምላሾች

በኦሮምያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ወስጥ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስድስቱ (ፍቼ፣ ፍቼ ቁጥር ሁለት፣ ጫገል፣ ሸራሮ፣ ውጫሌ፣ መቶኣለቃ ሃ/ማሪያም ገመዳ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ተመረጠው መረጃ ተሰበስቧል። ከሁሉም ተጠኚ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ሁለት መምህራን (አንድ ወንድ እና አንድ ሴት) በጥቅሉ ኣስራ ሁለት (12) መምህራን በአመቺነት ተመረጠው ከአማርኛ ጽህፈት ስህተት ጋር የተገናኘ ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸዋል። በአመችነት የተግኙ ስድስት ተማሪዎች ያሉበት አንዳንድ ቡድን ተመስርቶ የቡድን ውይይት ከተከናወነ በኋላ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ተወሰወዷል። ተጠኝዎች ለተጠየቁት ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሰች እና የቡድን ውይይቶች ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ።

4.1.2. የመምህራን ቃለ መጠይቅ የተጠቃለሉ መልሶች

ከከምህራኑ ጋር በተደረገው የገፅ ለገፅ መጠይቅ ውጤት እንደሚያስረዳው ተማሪዎች ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ በርካታ ከአናባቢዎች ጋር የተያያዙ ስህተቶችን እንደሚሰሩ ገልጸዋል። በተለይ ሳልስ /ኢ/ እና ሳድስ /እ/ አናባቢዎችን ሲጽፉ በጠቅላላ በሚያስብል መልኩ እያቀያሩ እንደሆነ ተናግረዋል። ከሌሉች ተነባቢዎች ኣናባቢዎችም ጋር የሚገናኝ በርካታ ስህተቶችን እንደሚሰሩ ወይም በተገቢው ሁኔታ እንደማይጽፉ አብራርተዋል። በክፍሉ ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተማሪዎች በኣማርኛ ቋንቋ ለመጻፍ እንደሚይቸገሩ ኣንዳንዶች ምንም መጻፍ አንደማይችሉ ገልፀዋል።

መምህራኑም ጽሁፋቸውን ሲያርሙ ከኣናባቢዎች ጋር ተያይዘው ለሚፈጠሩ ስህተቶች ትኩረት እንደማይሰጡ እንዲያውም ተከታትለው እንደማያርሙ ይናገራሉ። በአብዛኛው ከኣናባቢ ጋር የሚገናኙትን ስህተቶች እነማን እንደሆኑ እንደሚያቁ ኢአፍ-ፈት ተማሪዎቹ ከአናባቢዎች ጋር የሚሰሩትን ስህተቶች ተከታትለን ብናርም በጣም ብዙ ስህተቶች ከመሆናቸው የተነሳ የስነልቦና ጫና እንዳያድርባቸው በመፍራት ከአናባቢዎች ጋር የሚገናኙ ሰህተቶችን አለማረማቸውን ለጽሁፉ ይዘት እና አደረጃጀት ብቻ ውጤት እንደሚሰጡ ገልጸዋል። አንዳንዶቹ አናባቢም ሆነ ተነባቢ ፊደላትን አይለዩም በማለት ተማረው ነው የገለጹት።

በተጨማሪም መምህራኑ ሲገልጹ ስህተቱ ማለትም በቋንቋው ብቁ ተናጋሪ እና ጸሀፊ ያለመሆን ችግሩ የሁሉም ነው የሚያስብል ነው። በተለይ በኣማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በኣማርኛ ቋንቋ ያልተማሩ ተማሪዎች ችግር በጣም የጎላ ነው። አንዳንዶቹ ሆሄያትን የመለየት እና ቀላል የተባለውን ዘወትራዊ መግባቢያን ለመፍጠር የሚቸገሩ ናቸው። ከኣናባቢዎች (በተለይ ከሳልስ እና ከሳድስ) ጋር የተያየዙ

ችግሮችን በጭራሽ ማረም ትተናል መጠነኛ ይዘት ያለው ነገር ከነስህተቱም ቢሆን ከጻፉ ወይም ከተናገሩ ለዚያ ጉዳይ ብቻ ማለፊያ የሚሆን ውጤት እንሰጣለን። እያንዳንዱን ጉዳይ በህጉ መሰረት ተከታትለን እናርም ብንል ምናልባት ሁሉም ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ሊወድቁ ይችላሉ።

ለተማሪዎቹ በቋንቋ ክሂሎች (በተለይ ከፅሀፈት ጋር) ላይ ለሚያሳዩት ድክመቶች ምንጩ ከምን የተነሳ ነው በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡም የመጀመሪያው ምክንያት ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን ነው ይላሉ። አማርኛ ከማግባቢያ መሳሪያነቱ ባለፈ ፖለቲካው ከገዢ መደቦች እና ከጭቆና ጋር በመገናኘቱ ለችግሩ መጎልበት አስተዋጽኦ ያለው ይመስለናል በማለት ገልጸዋል።

በሁለተኛነት የሚነሳው ምክንያት ተማሪዎቹ ቋንቋውን ዘግይተው መማር መጀመራቸው ነው። ይህም ሲባል ኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን መማር የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል ነው። በተጨማሪም ለቋንቋው ትምህርት በሳምንት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት አነስተኛ መሆንና ለደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ደግሞ ሰፊ መሆን የመማር ማስተማር ሂደቱን በአግባቡ ለማከናወን የጊዜ እጥረት መግጠሙ ሌላኛው ምክንያት ነው። ይህ ተማሪዎቹ ቋንቋውን የሚለማደቡትን ጊዜ በጣም ይገድበዋል መይም በቂ ግዜ አያገኙም። በሌላ መልኩ የክሂልና የስነልሳን ትምህርቶች በተለይ በአማርኛ አፋቸውን ላልፈቱበት የክፍሉ ተማሪዎች ዘርዘር ባለ እና በተለየ መልኩ የተሰናዳ ማስተማሪያ ሊዘጋጅ ይገባል። ይሄ ጉዳይ በእንግሊዘኛው በስፋት ይሰራበታል። እንግሊዘኛ ለሁለተኛ ወይም ለውጭ ቋንቋ ተናጋሪ ሰለጣኞች የሚጠቀሙበት ማስተማሪያ መሳሪያ እና የሚመደበለት የማስተማሪያ ጊዜ ከኣፍ-ፈቶቹ የተለየ ነው።

4.1.3. የተማሪዎች ቃለ መጠይቅ እና ቡድን ውይይት መልሶች

በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ ተማሪዎች እንደሚገልፁት በኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት ከሳምንት ከኣንድ ከሁለት ቀን በላይ እንዳልተማሩትና በቋንቋው(አማርኛ) መግባባት እንኳ በወጉ እንደማይችሉ ቀደም ሲል ለተግባቦት በስፋት ሲገለገሉበት የነበረው ቋንቋቸው የኣፍ መፍቻቸው ብቻ እንደነበረ እና በአማርኛ ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቸገሩ ይገልፃሉ። የኣማርኛ ቃላት ፍቺን ለመረዳትም እንደሚያስቸግራቸው ተናግረዋል። ይህ ምላሻቸው በጻፉት ድርሰት ውስጥ ካለው ከአናባቢዎችጋር የተያያዙ በርካታ ስህተቶች ጋር ሲገናዘብ የጉዳዩን እውነትነት ያጎላዋል። የትምህርት ኣሰጣጡ ያለባቸውን በኣማርኛ የመጻፍና የመናገር ችግር በተገቢው መልኩ ሊቀርፍ ያልቻለ መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጸዋል። የክሂልም ሆነ የስነልሳን ትምህርቶች ማስተማሪያ ዘዴውም ቢሆን ስር የሰደደውን የኣማርኛ ቋንቋ ክሂሎች ችግር ሊቀርፍ

የሚችል እንዳልሆነ በኣማርኛ ሲጽፉም ሆነ ሲናገሩ ከኣናባቢዎች ጋር የተያያዙ ስህተቶችን መስራታቸውን እራሳቸውም እንደሚገነዘቡ ተናግረዋል። ጉዳዩን በተመለከተ አንድ ተማሪ ሀሳቡን ሲገልጽ

ከኣንደኛ ክፍል እስከ አራተኛ ክፍል በኣፋን ኦሮሞ መማሬ፤ የገጠር አካባቢ አማርኛ በስፋት የማይነገርበት ልጅ መሆኔ፤ ትምህርቶችን ሁሉ በኣፋን ኦሮሞ መማሬ፤ በማንኛውም ሁኔታ የአማርኛ ምርጫ አለመኖሩ በኣካባቢያችን ካሉ የከተማ ልጆች ጋር በአማርኛ ለመግባባት አለመሞከሬ ተጽእኖ አሳድሮብኛል። ትምህርቱን በጣም ተቸግሬ ነው የተማርኩት።

ሌላኛው ተማሪ ደግሞ ከታች የተማሩበትን ሁኔታ ሲገልጽ እንዲህ በማለት ነው፤

አማርኛ መማር የጀመርነው ከኣምስተኛ ክፍል ቢሆንም በደንብ አልተማርንም ክፈለጊዜውም በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። መምህራንም ትኩረት ሰጥተው አያስተምሩንም እኛም ትኩረት ሰጥተን አንማርም ነበር።አማርኛውን ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ በቂ መለማመጃ ጊዜ አልነበረንም። እኛም በአብዛኛው ኣማርኛውንም ስናጠና በራሳችን ቋንቋ እየተነጋገርን ነበር።

የተተኪሪ ቡድን ውይይት ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ከተመረጡት ዘዴዎች አንዱ ነው። የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የጀመርነው ዘግይተን ነው (ከኣምስተኛ ክፍል በኋላ) ። ለምንም አገልግሎት ይጠቅመናል ብለን አስበን አናውቅም ነበር። በአካባቢያችን በማንኛውም ሁኔታ የምንግባባው በራሳችን (በአፍ መፍቻ ቋንቋችን)ነው። ብዙዎች የአማርኛ አስተማሪዎቻችን የአካባቢው ተወላጆች ስለነበሩ አማርኛው ሲከብደን ይተረጉሙልን ነበር። ካናባቢ ንበት እንጻር አስተማሪዎቻችንም የተሰተካከለውን አጠራር አልነበረም የሚጠሩት።

ብዙዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካባቢያችን ሰዎች ወይም የኣካባቢውን ቋንቋ የሚችሉ ስለነበሩ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የምንነጋገረው በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ነበር። ብዙዎቹ በቋንቋው ያልሰለጠኑ ነበሩ፤ ውጤት ዝምብሎ ይሰጠን ነበር። ለአማርኛ መምህራንም ትኩረት አይሰጡትም ነበር እኛም ምንም አይመስለንም ነበር። እዚህ ግን በጣም ተቸግረንበታል። አሁንም ያን ያህል ብቁ ነን ብለን አናስብም ስንጽፍም ሆነ ስንናገር እንቸገራለን።

ከተማሪዎች ጋር የተደረገው የቡድን ውይይት እንደሚያመለክተው ተማሪዎች አማርኛን እንደዋና ትምህርት ሳይሆን እንደ ትርፍ ሲማሩ መቆየታቸውን፣ የተመደበለትም ክፍለጊዜ ትንሽ ባብዛኛው ኣንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ፣

ያንንም አብዛኛውን ክፍለ ጊዜ ለሌላ ትምህርት እና ለቤተ መጽሀፍት ማንበቢያነት ሲጠቀሙበት እንደነበር ገልጸዋል።

4.3.2. **ተጠኝዎች ለሙከራ እንዲጽፉ ከተደረጉት ድርሰቶች ላይ የተገኙ ስህተቶች ትንተና**

ሠንጠረዥ 1 ድርሰቶቹ ሲፃፉ የተፈፀሙ ስህተቶች ብዛት ዝርዝር መረጃዎች

	የትምህርት ቤት ስም	ተ/ቁ	የተማሪዎች ብዛት	የስህተቶች ብዛት
1	ሀ	9ኛ	25	728
		10ኛ	20	360
2	ለ	9ኛ	13	85
		10ኛ	17	202
3	ሐ	9ኛ	19	218
		10ኛ	20	511
4	መ	9ኛ	17	214
		10ኛ	16	392
5	ረ	9ኛ	24	242
		10ኛ	25	258
6	ሰ	9ኛ	13	625
		10ኛ	17	608
ጠቅላላ ድምር			226	4443

በምዕራፍ ሶስት የስህተት አተናተን ዘዴ ላይ እንደተገለፀው ስህተቶቹ በአይነት የተለዩትና የተመደቡት በቅድመ ምደባ የስህተት ምደባ ዘዴ ነው::ተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቶችን ሲፅፏቸው በዋናነት የተተኮረባቸው የስህተት ዓይነቶች ተፈላጊና መሰረታዊ የሆኑ አናባቢዎችን መተው፣ ለቦታው አስፈላጊ/ትክክል ያልሆኑ አናባቢዎችን በጽህፈቱ ስራ ውስጥ መክተት፣ማስገባት፣ የተያዘውን መሰረተ--ሃሳብ የሚያፋልሱ፣ትክክለኛ ያልሆኑ

አናባቢዎችን መምረጥና መጠቀም፣የተዛባ የአናባቢ ስርዓት መከተል እና ፍቺ ለይ የሆኑ አናባቢዎችን መጠቀም ስህተቶች ናቸው:: ከነዚህ ዋናዋና የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠረውን የስህተት መጠን ዝርዝር መረጃ እንደሚከተለው ለማስፈር ተሞክሯል::

በሰንጠረዥ አንድ በቀረበው መረጃ መሰረት በድርሰቶች ከተመደቡት የስህተት አይነቶች ከፍተኛ ስህተት የተቆጠረው ተፈላጊና መሰረታዊ የሆኑ አናባቢዎችን መተው ምድብ ውስጥ ነው:: በአጠቃላይ ከተገኙት 4443 ስህተቶች መካከል 2150 ያህሎቹ በዚህ ምድብ የተቆጠሩ ስህተቶች ናቸው:: የስህተቶች አይንትም ከተፈላጊና መሰረታዊ የሆኑ አናባቢዎችን መተው ቀጥሎ ከፍተኛ የስህተት መጠን የተገኘበት ምድብ የተያዘውን መሰረተ--ሃሳብ የሚያፋልስ ስህተት ነው:; ከተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ የተገኘው ስህተት 1942 ያህል ነው::

ስህተቶቹ የተለቀሙት ጥናቱ ከተከናወነባቸው (ፍቼ፣ፍቼ ቁጥር ሁለት፣ ጫገል፣ ሸረሮ፣ ውጫሌ፣ መቶኣለቃ ሃ/ማሪያም ገመዳ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ነው::

ለጥናቱ እንዲሆኑ ተመርጠው ከቀረቡላቸው ኣምስራት ርእሶች ውስጥ ወይም ሌላ በፍላጎታቸው ርእስ መርጠው እንዲጽፉ ከተደረገው አንቀጽ ውስጥ ነው። ለጥናቱ ከተመረጡት ሁለት መቶ ኣርባ ተማሪዎ ውስጥ ኣስራ ኣራቱ ምንም ያለጻፉ በመሆናቸው ከድርሰት ፈተናው እንዲቀሩ ተደርገው ሁለት መቶ ሃያ ስድስቱ የየራሳቸውን አንቀጽ ጽፈው አሰገብተዋል። በሁሉም ተማሪዎች በሚባል ደረጃ በድርሰቶቻቸው ውስጥ ስነልሳናዊ በርካታ ስህተቶች ተስተውለዋል። ሆኖም ኣጠቃላይ ስህተቶች በወፍ በረር ተቆጥረው ከሁለት ሺህ ኣንድ መቶ ሃምሳ በላይ ናቸው። አንዳንዶቹ ተጠኚ ተማሪዎች የጻፏቸው አንቀጾች ምን እንደሚሉ ለመረዳት የሚያዳግቱ ወይም ምንም መልእክት ማስተላለፍ የማይችሉ ሆነው ተገኝተዋል። ከተለያዩ አንቀጾች ተለቅመው ዋና ዋና ተብለው ለአብነት የተለዩት፤ ከአማርኛ አናባቢዎች ጋር የሚገናኙት ስህተቶች ተጠቃለው ሲቀመጡ የሚከተለውን ይመስላሉ።

⟶(2)/ኧ / /ኣ/

የተገኘው ስህተት	**መባል የተፈለገው**
ዳስታ /ድኣስትኣ/	ደስታ/ድኧስትኣ/
ይገማታል /ይግኧምኣትኣል/	ይገመታል/ይግኧምኧትኣል/

የምወዳድ /ይኧምውኧድኣድ/	የሚወደድ/ይኧምኢውኧድኧድ/

⟶(3)/ኧ / /ኤ/

የተገኘው ስህተት	**መባል የተፈለገው**
ሚዜና/ምዜና/ምኢዝኤንኣ/	ምዘና/ምእዝኧንኣ/
ተመስጌን/ተመስጊን	ተመስገን
አሌ /አልኤ/	አለ/አልኧ/

⟶(4)/እ / /ኢ/

የተገኘው ስህተት	**መባል የተፈለገው**
ወደፍት/ ውኧደኧፍት	ወደፊት/ውኧደኧፍኢት/
ጢቅት/ጥኢቅት/	ጥቂት/ጥእቅኢት
ሲሜጣ/ስምኤጥኣ/	ሲመጣ/ስምጥኣ;

⟶(5)/ኢ / /ኣ/

የተገኘው ስህተት	**መባል የተፈለገው**
ባህራ/ ብኣህርኣ/	ባህሪ /ብኣህርኢ/
ኣፉቃራ/ኣፍኡቅኣርኣ/	አፍቃሪ/ኣፍቅኣርኢ/
ሳሊፍ/ስኣልኢፍ/	ሲያልፍ/ስኢይኣልፍ/

(6)በ/እ / ወይም ከሳድስ ተነባቢዎች ቀጥሎ ሌሎች አናባቢዎችን ማስገባት

የተገኘው ስህተት	**መባል የተፈለገው**
ተናሼ/ትኧንኣሸኤ/	ታናሽ /ትኣንኣሸ/

የሚታሚር/ ይኽምኢትኣምኢር	የምታምር /ይኽምትኣምር/
የሚወዳው /ይኽምኢውኽድኣው/	የምወደው/ይኽምውኽድኽው/

ከላይ በተመረጡት -አማርኛ ቋንቋን በ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሚማሩ ተጠኚ ተማሪዎች ከጻፏቸው ኣንድ መቶ ሃያ ስድስት (126) አንቀጾች ውሰጥ በተደረገው ዳስሳ የተገኙት ከኣናባቢ ጋር የተገናኙ ስህተቶች ከሁለት ሺህ ኣንድ መቶ ሃምሳ በላይ ናቸው። እነዚህ ተመርጠው የቀረቡት ለአብነት ማሳያ እንዲሆኑ ተፈልጎ ነው። ተጠኚዎቹ በስፋት የፈጸሟቸው ከኣናባበ ጋር የተገኛኙት ስህተቶች ግእዝ ፣ ሳልስ እና ሳድስ ጋር የተገኛኙ ብቻ ሳይሆኑ የሌሎችንም አናባቢዎች ግድፈት ቅየራ እና ትክክቶሽ በስፋት ታይቷል። ይሁን እንጂ ከግእዝ፣ሳልስ እና ሳድስ ጋር የተገኛኙ ስህተቶች ከሌሎች አንጻር ሲገመገሙ በጣም ብዙ ናቸው። ይህ ሁኔታ በቋንቋው የሚደረገው ተግባቦት/ ግንኙነት ከማወኩም ባሻገር በኣማርኛ አናባቢዎች ገለጻ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል ምናልባትም ወደፊት በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች (በኩሽ፤ በኦሞቲክ እና በኣባያዊ ምድብ) ውስጥ የሌሉት አናባቢዎች /ኧ / እና /እ/ በኣማርኛም ውስጥ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ባንድ ወቅት የሉም ሊባልም ይችላል።

4.2. የግኝት መረጃ ትርጎማ

የሰው ልጅ አእምሮ እኛ ከምናስበው በላይ እጅግ በጣም ትክክል ነው። ሰዎች አእምሯቸውን ተጠቅመው በመፈላሰፍ የፈጠሯቸው በጣም ትክክል የምንላቸው ነገሮች ሁሉ፤ ዘመናዊውን ኮምፒዩተር እና በእሱ አማካኝነት የተፈጠሩት የዘመኑ የፈጠራ ውጤቶች ሁሉ ከአእምሮ አንጻር ሲታዩ ምንም ናቸው ወይም እጅግ በጣም ኢምንት ናቸው። ልዩ ልዩ ዘመናዊ የሰው ልጅ ፈጠራዎች አእምሮ ሊያከናውነው ከሚችለው ነገር ጋር ሲነጻጸሩ ፍጹምነታቸው ኢምንት ነው። እጅግ በጣም ይራራቃሉ። ቋንቋ የዚህ የረቂቁ አእምሮ ክፍል ውጤት ነው። የሰው ልጅ አእምሮ ቋንቋንም ሲያቀናብር ፍጹም ትክክለኛ በሆነ መንገድ ነው። ምናልባት የቋንቋው ሳይንስ /ስነልሳን ገና ቀርነት ስላለው የቋንቋ ገለጻችን ወጣ ገባ የሆነ እና ትክክለኝነቱ ፍጹም ያልሆነ ይሆናል። በቋንቋ አጠቃቀም ወቅት ስህተት የሚፈጠር ከሆነ ቋንቋውን የሚያቀናብረው አዕምሮ ተሳስቶ ሳይሆን ባንዳች ውጫዊ በሆነ ምክንያት ተጽእኖ ሊሆን ይችላል። የስነልሳን ባለሙያው ተግባር በተቻለ መጠን ያን ትክክል የሆነ የአዕምሮ የቋንቋን አደረጃጀት እና አቀነጃጀት ማሳየት ነው። የተግባራዊ ስነልሳን ወይም የቋንቋ ስነዘዴ/የቋንቋ ክሂል ባለሙያው ደግሞ የተፈጠሩ ስህተቶችን ነቅሶ ለይቶ ማውጣት እና ስህተቶች ለተፈጠሩበት ምክንያት በቂ የሆነ በስነልሳን ሳይንስ የተደገፈ ማብራሪያ መስጠት ነው።

በዚህ ጥናት ውስጥ የታዩት እጅግ በርካታ የሆኑ ከአናባቢ ጋር የተያያዙ ስህተቶች የተፈጠሩበት በቋንቋው አስቸጋሪነት ወይም ተማሪዎች ቋንቋውን ለመረዳት የሚያስችል ልዩ ሁኔታ ስላለባቸው አይደለም። ሌሎች ከቋንቋ መማር እና ማስተማር ጋር የተያያዙ በርካታ ስነልሳናዊ ችግሮች በሚያሳድሩት ጫና የሚከሰት ነው። እነዚህም

1. በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ ፤ ማለትም የሁለቱ ቋንቋዎች መዋቅር ገለጻ ልዩነት ለምሳሌ የአማርኛ አናባቢዎች ቁጥር ሰባት መሆኑ እና የሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋ ወገኖች (ኩሽ እና ኦሞቲክ ምድቦች)የአናባቢዎች ቁጥር በአብዛኛው አምስት መሆኑ ችግር ሊሆን ይችላል። ይህን በተመለከተ ሮች (1992) ሲገልጹ በአናባቢ ስህተቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አናባቢዎች ላይ የንበት ስህተት ሊፈጠር የሚችለው አንድም በሁለቱ ቋንቋዎች ውስጥ የሚገኙ የአነባቢዎች ቁጥር አለመመጣጠን አልያም አናባቢዎች በሚጠሩበት ወቅት ያለው የምላስ ወይም የአፍ እንቅስቃሴ በሚኖርበት ጊዜ ያለ የቅርጽ አለመጣጣም ነው።

2. ለቋንቋ ባለ አሉታዊ አመለካከት፤ አይጠቅመንም የሚል እሳቤ፣ የፖለቲካ ተጽእኖ፤ በቋንቋዎች መካከል ያለ ፉክክር

3. የቋንቋውን መዋቅር ለማስተማር የተጠቀመበት ዘዴ የተሳሳተ መሆን

4. የቋንቋውን ክሂሎች ለመማር እና ማስተማር የተጠቀመበት ስነዘዴ የተዋጣለት አለመሆን

5. ቋንቋውን ለመማር እና መስተማር የተመደበው ጊዜ አነስተኛ መሆን /በቂ ባለመሆኑ፤ተገቢ መለማመጃ ጊዜ አለመኖር

6. በቂ እና በተገቢው መንገድ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ቁሳቁስ አለመሟላት የመሳሰሉት ናቸው።

እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ በሌሎች ሰፊ አገልግሎት ባላቸው የአውሮፓ ቋንቋዎችም (እንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይና፣ ጀርመን ወዘተ) ቋንቋ ትምህርት ላይም ሊታይ የሚችል ተግዳሮት ነው።

ቋንቋዎች አገልግሎታቸው ሲሰፋ በተለያየ አካባቢ ቋንቋውን በአፍ-ፈትነት ለማይናገሩ ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ። ይህ ሁኔታ በሚፈጠርበት ወቅት እነዚያን ቋንቋዎች የሚያስተምሩት በቋንቋው አፍ-ፈት የሆኑ እና በዚያ ሙያ የሰለጠኑ ብቻ መሆናቸው ይቀርና፤ ያንን ቋንቋ በትምህርት ያገኙ/የሰለጠኑ በሌላ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ሁሉ የቋንቋው መምህራን ወይም ባለሙያ ይሆናሉ።

ይህ ተሞክሮ በኣለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ግልጋሎት ወይም ሽፋን ባላቸው የአውሮፓ ቋንቋዎች እንደ እንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ እና ፖርቹጋል በመሳሰሉት ቋንቋዎች ዘንድ በስፋት የተለመደ እና ሲተገበር የነበረ አሁንም ያለ ጉዳይ ነው። ስለዚህም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ተከናውነዋል። ለአብነት የተወሰኑትን እንጥቀስ ኢራን ውስጥ በተለያየ ደረጃ እንግሊዘኛ የሚያስተምሩ መምህራን ላይ በነህቢብ ጎዋሀሪ እና ሌሎች (2016 እዜአ) የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ጫና የሚያርፍባቸውን፣ ዝቅተኛ ቅላጼ እና አጭር የግዜ እርዝማኔ ያላቸውን አናባቢዎች በመግደፋቸው እና የንበት ልዩነት በማስከተሉ ቋንቋውን ለማስተማር ችግር እንደሆነ ተገልጧል። ሙሐመድ (2013) በአረብኛ አፍ-ፈት የሆኑ አረብኛ ተናጋሪዎች እንግሊዘኛን ሲያነቡ የሚሰሯቸው ስህተቶች እና የውስጥ ቋንቋ ጣልቃገብነትን ችግር አጥንቷል። ሁዋኝ (2015) ባደረገው የሙከራዊ ሰነድምጽ ጥናት ቻይናዊያን እንግሊዘኛ በሚናገሩበት ወቅት አናባቢዎቹን ሲጠሩ የሚፈጥሩትን ስህተት ተመልክቷል። በኣፍ ቅርጽ ልዩነት፤ በኣናባቢዎች ርዝመት እና እጥረት የፍች ልዩነት ማስከተላቸውን አሳይቷል።

በኣማርኛ ቋንቋ ንግግርም ሆነ ጽህፈት ውስጥ ከኣናባቢ ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ስህተቶች፤ አናባቢዎች በመቀያየራቸው፣በመገደፋቸው እንዲሁ በቀላሉ እንደ ምላስ ወለምታ በመቁጠር ሊተው የሚችሉ አይደሉም። የኣናባቢ ለውጥ በመደረጉ ወይም በመገደፉ በቃሉ ላይ የፍች ለውጥ ስለሚያስከትል በተግባቦት ላይ ችግር ይፈጥራል። ሊባል የተፈለገው መልእክት ቀርቶ ያለተፈለገው ሌላ መልእክት ሊተላለፍ ይችላል።

ለምሳሌ፤ ስል≠ ሰል≠ ሲል ፣ቢል ≠ በል ≠ባል፣ የምመጣው ≠ የሚመጣው ≠ የማይመጣው፣ የሚሞት≠ የምሞት ≠ የማይሞት፣ የምበላው ≠ የማበላው≠ የሚበላው ≠ የማይበላው።

እነዚህን አይነት እና ከነዚህም የባሱ የቃለቱን ፍች ከናካቴው የሚያጠፉ ስህተቶች በጥናቱ ውስጥ በስፋት የታዩ ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ የቋንቋ ሁነኛ ተግባር የሆነውን ተግባቦት አስተጓጉሎ ወይም ያልተፈለገ ፍች ፈጥሮ ያልተጠበቀ ችግር ከመፍጠራቸውም በላይ የአማርኛን የኣናባቢዎች ሣይንሳዊ የመዋቅር ገለጻ ሊያዛቡት ይችላሉ።

5. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ኣሰተያየት

5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ባሁኑ ወቅት በአማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ በኦሮምያ ሰሜን ሸዋ ዞን የአማርኛ ቋንቋ የሚማሩ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች በኣማርኛ ሲጽፉ የሚፈጥሯቸውን ስህተቶችን በማውጣት ወቅታዊ የሆነ ስነልሳናዊ ትንተና መስጠት ነው።

በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ ተጠኚዎች በ2015 ዓ.ም. በኦሮምያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ወስጥ የሚገኙ የስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትህርት ቤቶች (9ኛ እና 10 ክፍል) ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች ከጻፏቸው 126 (ኣንድ መቶ ሃያ ስድስት) አንቀጾች ውሰጥ በተደረገው ዳስሳ የተገኙት ስህተቶች ሲጥቃለሉ የሚከትለውን የመስላሉ። ፍች የማይሰጡ ቃላት ማሰግባት፣የሰዋስወ ኣግባብ ኣለምጣጣም፣ የሆሄያት ገድፈት እና ከተነባቢና ከኣናባቢ ጋር የተገናኙ ስህተቶች ከኣራት ሺህ ኣምስት መቶ ሃምሳ በላይ ናቸው። ተጠኚዎቹ በስፋት የፈጸሟቸው ከኣናባቢ ጋር የተገኛኙት ስህተቶች ግእዝ ፣ ሳልስ እና ሳድስ ጋር የተገኛኙ ብቻ ሳይሆኑ የሌሎችም አናባቢዎች ግድፈት ቅዬራ እና ትክክቶሽ በስፋት ታይቷል። ይሁን እንጂ ከግእዝ ፣ ሳልስ እና ሳድስ ጋር የተገኛኙ ስህተቶች ከሌሎች አንጻር ሲገመገሙ በጣም ብዙ ናቸው። ይህ ሁኔታ በቋንቋው የሚደረገው ተግባቦት ከማወኩም ባሻገር በኣማርኛ አናባቢዎች ገለጻ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል ምናለባትም ወደፊት በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች (በኩሽ፤ በኦሞቲክ እና በኣባያዊ ምድብ) ውስጥ የሌሉት አናባቢዎች /ኧ / እና /እ/ በኣማርኛም ውስጥ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ባንድ ወቅት የሉም ሊባልም ይችላል።

ከጥናቱ የተገኘው መረጃ ተፈትሾ፣የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በአማርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ያልሆኑ ተጠኚ ተማሪዎች በሚጽፏቸው አንቀጾች ከአናባቢዎች ጋር የተያያዙ በርካታ ስህተቶች አሉባቸው። በተለይ ከሳድስ /እ/ እና ሳልስ /ኢ/ ጋር የተገናኙ ስህተቶች በጣም ብዙ ናቸው።ዋና ዋናዎቹ /እ/እና/ኢ/ በሌሎች ኣናባቢዎች መተካት ወይም መግደፍ ናቸው። ከነዚህ ባለፈ ከ14 በላይ የሚደርሱ ከኣናባቢዎች ጋር የሚገናኙ /የተየያያዙ የስህተት ኣይነቶች እነደሚፈጥሩ ከጻፏቸው አንቀጾች እና በቃለመጠይቅ ወቅት ያደርጉት ከነበረው የቃላት ልውውጥ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በብዛት የተከሰቱት ከኣማርኛ ኣናባቢዎች ጋር የሚገናኙት ስህተቶች ፤ ኣናባቢዎችን በማቀያየር ረገድ /እ/ — /ኢ/፣ /ኢ/ — /ኤ/፣ /ኤ/—/ኢ/፣ /ኧ/—/ኣ/፣ /ኧ/ —/ኤ/ ፣ /ኧ/ — /ኡ/፣ /ኦ/ — /ኣ/፣ /ኦ/ —/ኧ/ ዋናዋናዎች ሲሆኑ፤ የሚገደፉ እና አለቦታቸው የሚገቡ ኣናባቢዎችም ኣሉ። እነዚህም /እ/ እና /ኢ/ በብዛት ይገደፋሉ፤ /ኢ/፣/ኣ/እና /እ/ አለቦታቸው ይገባሉ። እንዲሁም /እ/ እና /ኧ/ በሌላ ኣናባቢ ይተካሉ። እነዚህ ስህተቶች ደግሞ ተግባቦት ከማወክም አልፈው ፍቺውን መረዳት የሚያዳግቱ ናቸው።

በዚህ ጥናት ውስጥ የታዩት እጅግ በርካታ የሆኑ ከአናባቢ ጋር የተያያዙ ስህተቶች የተፈጠሩበት በቋንቋው አስቸጋሪነት ወይም ተማሪዎች ቋንቋውን ለመረዳት የሚያስችል ልዩ ሁኔታ ስለሌላቸው አይደለም። ሌሎች ከቋንቋ መማር እና ማስተማር ጋር የተያያዙ በርካታ ስነልሳናዊ ችግሮች በሚያሳድሩት ጫና የሚከሰት ነው። እነዚህም:- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ፣ ለቋንቋው ባለ አሉታዊ አመለካከት፤ የፖለቲካ ተጽእኖ፤ በቋንቋዎች መካከል ያለ ፉክክር፣ የቋንቋውን መዋቅር ለማስተማር የተጠቀመበት ስነዘዴ የተሳሳተ መሆን፣ የቋንቋውን ክሂሎች ለመማር እና ማስተማር የተጠቀመበት ስነዘዴ የተዋጣለት አለመሆን፣ ቋንቋውን ለመማር እና ማስተማር የተመደበው ጊዜ አነስተኛ መሆን፣ እና ለትምህርቱ የሚሆን በተገቢው መንገድ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ቁሳቁስ አለመሟላት የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው ናቸው።

5.2. ኣስተያየት

በኣንድ ቋንቋ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የተማሩ ተማሪዎች የሚጽፏቸውን ወይም የሚናገሯቸውን የአማርኛ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች በተገቢው መንገድ ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ተማሪዎች በተቃራኒው ምን እንደሚል የማይገባ፣ ለመረዳት የሚያስቸግር ወይም ሌላ ፍች የሚያስተላልፍ አረፍተ ነገር እና አንቀጽ የሚጽፉ ከሆነ በመርህ ግብሩ በርካታ ልፋት እና ብዙ ወጪ ተደርጎበት የተከናወነው ተግባር መክኗል ወይም አላግባብ የተለፋበት ከንቱ ድካም ሆኗል ማለት ነው። ስህተቱን እራሳቸውም ስለሚፈጽሙት በስህተትነት ለይቶ ማውጣትና ማስተካከል አይችሉም። ስለዚህ በቋንቋ ትክክለኛ ሰልጣኝ ሆነው ተገቢውን እውቅት እና ክህሎት እንዲያገኙ ከተፈለገ የሚከተሉት ሁኔታዎች በኣግባቡ ሊስተናገዱ ይገባል።

- የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ የሚያሳድር ከሆነ፤ማለትም የሁለቱ ቋንቋዎች መዋቅር ገለጻ ልዩነት ለምሳሌ የአማርኛ አናባቢዎች ቁጥር ሰባት መሆኑ እና የሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋ ወገኖች (ኩሽ ምድቦች)የአናባቢዎች ቁጥር በአብዛኛው አምስት መሆኑ ችግር ሊሆን ከቻለ፤ የስነልሳን መምህራን የተለያዩ የአናባቢዎችን ገለጻ እያነሱ በመካከላቸው ስላለው ልዩ ሁኔታ በዝርዝር ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ ቢመቻች

- ስለቋንቋ ባለ አሉታዊ አመለካከት፤ አይጠቅመንም የሚል እሳቤ፣ የፖለቲካ ተጽእኖ፤ በቋንቋዎች መካከል ካለ በመሀል ያለው ፉክክር ቀርቶ ቋንቋ በማግባባት ተግባሩ ብቻ ተገቢ ተግባሩን የሚወጣበት ዘዴ ቢቀየስ፣

- የቋንቋውን መዋቅር ለማስተማር የሚጠቀሙበት ስነዘዴ ትክክለኛውን የስነልሳን ገለጻ የተከተለ ቢሆን

- የቋንቋውን ክሂሎች ለመማር እና ማስተማር የሚጠቀሙበት ስነዘዴ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር የተዋጣለት እና ተገቢ የስነዘዴ አይነት ቢሆን፤
- ቋንቋውን (ክሂሎችን) ለመማር እና ማስተማር የተመደበው ጊዜ አነስተኛ ባይሆን /ተገቢ መለማመጃ ጊዜ ቢኖር፣
- በተለይ ኣንደኛ ደረጃ በሌላ ቋንቋ ተምረው በኣማርኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በቂ እና በተገቢው መንገድ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ቁሳቁስ ቢሟላ።

ዋቢ ፅሁፎች

ደብሬ ተሰማ። (1990)። “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና”. ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

Ackner, W. (2000). Error and Corrective Feedback: Updated Theory and Classroom Practice, *English Teaching Forum,* XXXIII, No.2, p.38.

Al-Buainain, H. (2005). Students' Writing errors in ESL: A Case Study, Quatar: Department of Foreign Languages, Qatar University.

BayeYimam. 2008. *Modern Amharic Grammar (*ዘመናዊየአማርኛሰዋስው*)*. 2nd edition. Addis Ababa: Elleni Printers, Private Ltd. Co.

Bereiter, C. & Scardamalia, M. (1987). The psychology of written composition.Hillsdale, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Boss, M.N. (2005). English Language Teaching (ELT) for Indian Students. Chennai: New Century Book House.

Brown, H.D. (1994). Principles of Language Learning and Teaching. Englewood Cliffs,

N.J: Prentice- Hall.

Burns, B. (1999). How to Teach Balanced Reading & Writing. Arlington Heights, IL: Skylight Professional Development.

Celce-Murcia, M. (2002). Language Teaching Analysis, London: Longman.

Chen, H. C. (1998). A contrastive analysis of the language errors made by the Chinese students of English as a second/foreign language. Journal of Wu-Feng Applied Linguistics, 6, 224-237.

Cheng, P. (2001). *Handbook of research in second language teaching and learning*. Mahwah, N.J.: L. Erlbaum Associates.

Corder, S. P. (1974). Error Analysis. In J. P. B. Allen and S. Pit Corder (eds.) Techniques in Applied Linguistics (The Edinburgh Course in Applied Linguistics: 3), London: Oxford University Press (Language and Language Learning), pp. 122-154.

---------- (1976). The Significance of Learner's Errors. *IRAL,* 5, 161-170.

---------- (1983). Error Analysis. New York: Oxford University Press.

Dulay, H. and Burt, M. (1977). "Remarks on creativity in language acquisition". In M. Burt, H.Dulay and M. Finocchiaro (eds.), Viewpoints on English as a Second Language. New York: Regents.

Dullay, et al., (1983). Error Analysis in Language Two, New York: Oxford University Press.

Edege, A. (1998). Writing Errors in Second Language Acquisition, Hilsdale, NJ: Lawrence Erlbaum.

Ellis, H. C. (1965). The Transfer of Learning. New York. The Macmillan Company.

Ellis, R. (1990). Instructed Second Language Acquisition. UK: Basil Black Well.

---------- (1997). SLA Research and Language Teaching. Oxford: Oxford University Press

Erdogan, V. (2005). Contribution of Error Analysis to Foreign Language Teaching. *Mersin University Journal of the Faculty of Education,* 2, 261-

Krashen, Stephen (2004). Applying the Comprehension Hypothesis: Some Suggestions . Presented at 13th International Symposium and Book Fair on Language Teaching (English Teachers Association of the Republic ofChina), Taipei, Taiwan, November, 13, 2004.

Ladefoged, P., and I. Maddieson. 1996. *The Sounds of the World's Languages*. Oxford: Blackwell

Littlewood, W. (1984). Foreign and Second Lagrange Learning. Cambridge, Cambridge University Press.

Norrish, J. (1983). Language Learners and their Errors, London: Modern English Publications.

Richards et al. (1992). Dictionary of language teaching and applied linguistics. Esex: Longman.

Richards, J. C. & Renandya, W. A. (eds) (2002) Methodology in Language-teaching: An Anthology of Current Practice. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. (1974). A nonconstructive approach to error analysis. *English Language Teaching Journal*. 25, 204-219.

Vanhove Jan and Irmtraud Kaiser (2011). Second-language acquisition research on critical period effects: caveats and statistical fallacies Department of Multilingualism, University of Fribourg, Switzerland.